# ሽግግር - የትምህርት ቤት አዎንታዊ ጅማሬ

**ቤተሰቦች የሽግግር ትምህርት እና የእድገት የጽሁፍ ማስረጃን ሲሞሉ የሚረዱ መመሪያዎች**

## በትምህርት ቤት ውስጥ መልካም ጅማሬ ለምን ያስፈልጋል?

አዎንታዊ የትምህርት ጅማሬ፡ ልጅዎ ከመዋእለ ህጻናት ወደ ትምህርት ቤት በሚሸጋገርበት ወቅት እና ለወደፊትም ቢሆን በተሻለ መንገድ እንዲማር እና ይበልጥ ደስተኛ እንዲሆን ሊረዳው ይችላል። በተጨማሪም፡ ልጅዎ እስከአሁን ካካበተውና የአሁን ተመክሮዎቹን በመገንባት ደህንነት፡ የራስ መተማመን እና ከማህበረሱም ትሥሥር እንዲያዳብር ይሄ አዎንታዊ የሆነ የሽግግር የመማሩን እና የማደጉን ሂደት ያስቀጥሎዋል። በተጨማሪም አዎንታዊ የትምህርት ጅማሬ ይበልጥ ጠንካራ እንዲሆኑ ሊረዳቸው ይችላል።

## የሽግግር ትምህርት እና የእድገት የጽሁፍ ማስረጃ ምንድን ነው?

የልጅነት እንክብካቤ አገልግሎቶች, ትምህርት ቤቶች፤ ከትምህርት ሰዓት ውጭ እንክብካቤ ሰጪ (OSHC/ኦ ኤስ ኤች ሲ) አገልግሎቶች እና ቤተሰቦች ለልጆች መማር እና የደህንነት ድጋፍ ለመስጠት አብረው ይሰራሉ። የሽግግር ትምህርትን እና የመሻሻል ጽሁፋዊ መግለጫ (TLDS/ቲ ኤል ዲ ኤስ) በመጠቀም መረጃዎችን ያጋሩ። ይህ የሚጻፈው ለእያንዳንዱ ልጅ ትምህርት ቤት በሚገባበት ጊዜ በልጅነት(ኢርሊ ቻይልድሁድ) አገልግሎት የሚቀርብ ነው።

TLDS በልጅነት አገልግሎት እና በትምህርት ቤቶች ጊዜ መካከል ስለ ልጅዎ መማር፤ እድገት መሻሻል እና ደህንነት መረጃን ያጋራል። ቲ ኤል ዲ ኤስ የልጅዎን ፍላጎቶች፤ ክህለቶች እና ችሎታዎች በአጭር እይታ ያቀርባል እናም ልጅዎን ለመደገፍ የግለሰብ አቀራረቦች እና የማስተማሪያ ስልቶችን በማቅረብ ይለያል።

ቲ ኤል ዲ ኤስ ልጅዎ ትምህርት ሲጀምር የሚማረውን ትምህርት ለመረዳትና ለመደገፍ ሊረዳዎት ይችላል። በ TLDS ውስጥ ያለው መረጃ የመሰረተ ትምህርት መምህራን ልጅዎን እንዲያውቁ እና ተገቢውን የማስተማሪያ መርሃ ግብሮች ለማቀድ ያግዛል። ልጅዎ በ ኦ ኤስ ኤች ሲ/OSHC ውስጥ ከሆነ TLDS ከዚያም ጊዜያቸውን ለማመቻቸት ይረዳል።

TLDS  የልጅዎን ስም፣ የልደት ቀን እና ፎቶ እንዲሁም የእርስዎን ስም እና አድራሻ መረጃ ጨምሮ አንዳንድ የግል ዝርዝር መረጃዎች አሉት። ሰነዱ በልጅነት ትምህርት ልጅዎን ሲረዱ የቆዩ ባለሞያዎች ስም እና አድራሻቸውም ሊይዝ ይችላል።

ትምህርት ከመጀመሩ በፊት እርስዎም ሆኑ ልጅዎ በ ቲ ኤል ዲ ኤስ ዝግጅት አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ልጅዎ ወደ ትምህርት ቤት ለማሸጋገር የሚያስችል አንዱ ስራ ነው።

## የልጄን TLDS እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

የልጅዎ የልጅነት አገልግሎት (ኢርሊ ቻይልድሁድ ሰርቪስ)ቲ ኤል ዲ ኤስ ኦንላይን ጋር ያገናኝዎታል። የኦንላይን TLDS ቲ ኤል ዲ ኤስን ለማጠናቀቅ በጣም ጥሩ የሆነ መንገድ ነው።.

በኦንላይን ኢንተርኔት መሳሪያን መጠቀም ካልቻሉ በምትኩ የወረቀት ቅጂ መጠየቅ ይችላሉ።

## የትኛውን የTLDS ክፍል ነው የምሞላው?

*ክፍል 1 እና 1.1* በልጅዎ የልጅነት ጊዜ አስተማሪ ይሞላሉ።

*ክፍል 1.2* ልጅዎ የእድገት መዘግየት ወይም የአካል ጉዳት ካለበት በልጅዎ የልጅነት ጊዜ አስተማሪ ሊጠናቀቁ ይችላሉ። ልጅዎን የሚረዱ ሌሎች ባለሙያዎችም በዚህ ረገድ ሊጨምሩ ይችላሉ።

*ክፍል 2 ልጁ* በደንብ በሚያውቁት አዋቂ ልጅዎ ይጠናቀቃል። ይህ እርስዎ ወይም የልጅነት ጊዜ አስተማሪያቸው ሊሆን ይችላል።

*ክፍል 3: ቤተሰብ* እርስዎ የሚሞሉት ነው። የሚያቀርቡት አስተያየት በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ ክፍል የልጅዎን ፍላጎት እንዲሁም በትምህርት ቤት ስለ ልጅዎ ያለዎትን አስተሳሰብና ተስፋ እንድትጋሩ የሚረዷችሁ ጥያቄዎች አሉት። ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ መስጠት መምህራን እና OSHC ሰራተኞች (ተግባራዊ ከሆነ) ለልጅዎ ምላሽ እንዲሰጡና እንዲረዱ ያግዛል። ይህ ደግሞ የመማር እና የእድገት ሂደት ይደግፋል።

## TLDS ከተጠናቀቀ በኋላ ምን ይደረጋል?

TLDSን ከጨረሱ በኋላ, በልጅነት ጊዜ አስተማሪዎ የተጠናቀቀ ቅጂ ይሰጥዎታል።

በልጅነት ጊዜ አስተማሪዎም የተጠናቀቀውን TLDS ከልጅዎ ትምህርት ቤት እና OSHC አገልግሎት ጋር ያጋራል (ተግባራዊ ከሆነ)።

ልጅዎ በየትኛው ትምህርት ቤት እንደሚማር እርግጠኛ ካልሆኑ የልጅነት ጊዜ አስተማሪዎ TLDS የተባለውን የጽሁፍ ሁለተኛ ቅጂ ይሰጥዎታል። ልጅዎን በሚያስመዘግቡበት ጊዜ ይህን ለትምህርት ቤቱ መስጠት ይችላሉ።

ክፍል 3 የቤተሰብን *ካላጠናቀቁ* የልጅዎ የልጅነት ጊዜ አስተማሪ አሁንም የተጠናቀቁትን ክፍሎች ከትምህርት ቤቱ እና ከOSHC አገልግሎት ጋር (ተግባራዊ ከሆነ) ያካፍላል እናም የሚጋራውን ቅጂ ይሰጥዎታል።

ከትምህርት ቤቶች የተገኘው የጥናትና አስተያየት ውጤት ይህንን መረጃ ለሌሎች ማካፈል ልጆች ወደ ትምህርት ቤት በተሳካ ሁኔታ እንዲሸጋገር እንደሚረዳ ያመላክታሉ። TLDSን ለልጅዎ ትምህርት ቤት ማካፈል ካልፈለጉ፤ እባክዎ ከልጅዎ የልጅነት ጊዜ አስተማሪ ጋር በዚህ ጉዳይ ላይ ተወያዩበት።

ተገቢ እና አስተማማኝ መረጃ የቪክቶሪያን ትምህርት እና እንክብካቤ ባለሙያዎች የልጆች ጤንነትና እና ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስፈልገውን እውቀት እና መረጃ እንዲያገኙ ይረዳቸዋል።

ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ [https://www.vic.gov.au/information-sharing-schemes-and-the-maram-framework](https://www.vic.gov.au/information-sharing-schemes-and-the-maram-framework)

## ለተጨማሪ መረጃ

ተጨማሪ እውቀት ለማግኘት በ [www.vic.gov.au/transition-school-resources-families](http://www.vic.gov.au/transition-school-resources-families) ገብቶ ማየት ይችላሉ።

ይህ መረጃ በበርካታ የማህበረሰብ ቋንቋዎችም በተመሳሳይ በድረገጽ ይገኛል፡ [www.vic.gov.au/transition-school-resources-families](http://www.vic.gov.au/transition-school-resources-families)